# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 282 መስከረም 24 2006 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን የወያኔ ወታደራዊና የስለላ ሞኖፖሊ መስበር የሥራው አንድ አካል አድርጎ ይመለከታል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ አምባገነኑን ወያኔ በመገዳደር ላይ ያሉትን ወገኖች ትግል ያደንቃል። እንዳንዳንዳችን የየበኩላችን ጥረት ካደረግን የኢትዮጵያን የመከራ ጊዜ በእጅጉ እንደምናሳጥር ያምናል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

ግዜ

## ግንቦት7 የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ለወገኑ ነጻነት የሚቆምበትን መንገድ እያዘጋጀ መሆኑን ገለጸ

ግንቦት ሰባት የፍትህ፤የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በወያኔ የዘረኝነት አለንጋ የሚለበለበዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት እራሱንና ወገኑን ነጻ የሚያደርግበትን መንገድ መከላከያ ሰራዊቱ ዉስጥ እየቀየሰ መሆኑን የንቅናቄዉ ዋና ጸሀፉ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ተናገሩ። ዋና ጸሀፊዉ ይህንን የተናገሩት ኖርዌይ ዋና ከተማ አስሎ ዉስጥ የግንቦት ሰባት ኃይሎችን ለመርዳት በተደረገዉ የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ላይ ባሰሙት ንግግር ነዉ። አቶ አንዳርጋቸው የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅቱን አስመለሰክተዉ ባደረጉት ንግግር እንደዚህ አይነቱ ወገናዊ ዝግጅት በአንድ በኩል በግንቦት7 ህዝባዊ ሀይል አባላት ዉስጥ ከፍተኛ መነቃቃት የሚፈጥር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ወራዊቱ የተጣለበት ህዝባዊ አደራ ምን ያክል ከፍተኛ መሆኑን የሚያስታውሰን ነው ብለዋል።

በቅርቡ ከኢትዮጵያ አየር ሀይል ከድተው ህዝባዊ ሰራዊቱን ስለተቀላቀሉት ጀግኖች ተጠይቀዉ በሰጡት መልስ የአየር ኃይል አባላቱ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ገልጸዉ ንቅናቄያቸዉ በመከላከያ ሰራዊት፤ በደህንነት መስሪያ ቤትና በመንግስት የጸጥታ ሀይሎች ዉስጥ ወያኔ ሊደርስበት በማይችልበት መልኩ የግንኙነት መስመር እየዘረጋ መሆኑን ገልጸዋል።

ኖርዌይ አስሎ ዉስጥ የተካሄደዉን አይነት የግንቦት ሰባት ኃይሎች የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት በሌሎች አገሮችና ከተሞች ዉስጥ ለማድረግ እቅድ አላችሁ ወይ ተብለው የተጠየቁት አቶ አንዳርጋቸው፣ ህዝባዊ ሀይሉ ከተግባር ጋር በተዛመደ መልኩ የገቢ ማሰባሰብ ዝግጅት መርሀ ግብሩን ይፋ እስከሚያደርግ ድረስ በህዝባዊ ሀይሉ ወይም በግለሰቦች ስም ምንም (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አገር ያለማል ተብሎ መሬት የተቸረዉ የህንዱ ካራቱሬ ከንግድ ባንክ የወሰደዉን ብድር አለመክፈሉ ተሰማ

ኢትዮጵያ ዉስጥ በግብርናዉ መስክ የሚታየዉን የሰዉ ኃይል ብክነትና በአጠቃላይ የአገሪቱን የምግብ እጥረት ችግር ይቀርፋል በሚል የወያኔ አገዛዝ ጋምቤላ ዉስጥ ልክ የሌለዉ ለምለም መሬት የሸለመዉ የህንዱ ካራቱሬ አግሮ አንዱስትሪ ኩባንያ ከአገር ዉስጥ ባንኮች የተበደረዉን ብድር አለመክፈሉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ትልቅ የመነጋገሪያ አርዕስት ሆኖ መሰንበቱ ታወቀ። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የአገሪቱን የካፒታል ችግር ያቃልላል ተብሎ ሰፊ መሬት የተሰጠዉ ካራቱሬ ኩባንያ ጭራሽ ከአገር ዉስጥ ባንኮች የተበደረዉን ገንዘብ ባለመክፈል የካፒታል እጥረት እየፈጠረ መሆኑ ገና ከጅምሩ የወያኔን የመሬት ቅርምት ፖሊሲ ይቃወሙ የነበሩትን አያሌ ኢትዮጵያዉያን አስቆጥቷል። በጋምቤላ ክልል ከ300 ሺ ሄክታር ያላነሰ መሬት በነጻ በሚባል ዋጋ የተረከበው የህንዱ የእርሻ ኩባንያ ካራቱሬ፣ በተሰጠው መሬት ላይ የልማት ስራ አለማከናወኑንና ከባንክና ከሌሎች አበዳሪ ድርጅቶች የተበደረዉን ዕዳ ለመክፈል አለመቻሉን አገር ዉስጥ የሚታተወመዉ ሰንደቅ ጋዜጣ ዘግቧል።

የህንዱ ኩባኒያ ካራቱሪ በታህሳስ 2003 ዓም ከኢትዮጵያ ንድግ ባንክ የወሰደዉን የ62 ሚሊየን ብር ብድር መክፈል በሚገባው ጊዜ ሊከፍል አልቻለም። ብድሩንም ለማስታመም የተደረጉ ተጨማሪ ጥረቶች ባለመሳካታቸው ጉዳዩ ወደህግ ክፍል መመራቱን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የንግድ ስራ ማስፋፊያ ክፍል ተጠባባቂ ሃላፊ የሆኑት አቶ ኤፍሬም መኩሪያ ለሰንደቅ ጋዜጣ በሰጡት ጋዜጣዊ ቃለ መጠይቅ ተናግረዋል። አቶ ኤፍሬም አክለዉ እንደገጹት ባንኩ በአሁኑ ወቅት የካራቱሬን ብድር የተበላሸ ወይንም መመለስ የማይችል እንደሰየመዉና ብድሩን ለማስመለስ ከፍርድ ቤት ሌላ አማራጭ እንደሌለለ ተናግረዋል።

የካራቱሬ የምርት መሳሪዎች ዋና ክፍል ኃላፊና የሠራተኞች ተወካይ የሆኑት አቶ አለምሰገድ አያሌው ኩባንያው 300ሺ ሄክታር መሬት ለማልማት ከግብርና ሚኒስቴር መሬት ተረክቦ የነበረ ቢሆንም ባለፉት አምስት አመታት ማልማት የቻለዉ ከ800 ሄክታር ብቻ እንደሆነ ተናግረዋል። ድርጅቱ 150 ያህል ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች እንዳሉት የገለጹት አቶ አለምሰገድ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ ከባድ የጦር መሳሪያዎችን ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ በማጓጓዝ ስራ መጠመዱ ተሰማ

ከአዲስ አበባ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የሚወስዱ አዉራ መንገዶች ታንኮችን፤ መድፎችንና ሌሎችም ከባድ የጦር መሳሪያዎችን በተሸከሙ ከባድ ወታደራዊ የጭነት ማመላለሻ ከሚዮኖች እየተጨናነቁ መሆኑን ኢሳት ቴሌቪዥንና ሬድዮ የአይን እማኞችን ጠቅሶ ዘገበ። ወያኔ ከኤርትራ ጋር ባለበት የድንበር አተካሮ ብዙም ዉጥረት በማይታይታይበት በአሁኑ ወቅት የጦር መሳሪያዎቹን በዚህ ደረጃ ለማንቀሳቀስ ለምን እንዳስፈለገ ብዙም የሚታወቅ ነገር ባይኖርም አንዳንዶች ወይኔ ሀይሉን ለማሳየት የሚያደርገዉ ከንቱ የእዩኝ እዩኝ ዘመቻ ነዉ ሲሉ ሌሎች ደግሞ በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ ከቀን ወደ ቀን እያየለ የሚጣዉን የአማጽያን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ነዉ ይላሉ። ያም ሆነ ይህ ወታደራዊ እንቅስቃሴዉን አስመልክቶ ከአገዛዙ ባለስልጣናት የተሰጠ መግለጫ ካለመኖሩም በላይ ሦስተኛ አካላት ጉዳዩን ለማጣራት ከመንግስት ጋር ያደረጉት ግንኙነትም ፍሬ አልባ ሆኗል።

ሰሜን ኢትዮጵያ ትግራይ፤ ጎንደርና አፋር ዉስጥ የወያኔን ስርዐት በኃይል ለመናድ የሚንቀሳቀሱ አያሌ መሳሪያ ያነገቡ ድርጅቶች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ላለፉት ሃያ አመታት በተናጠል ወያኔን የተዋጉ ኃይሎች ከቅርብ ግዜ ወዲህ የጋራ ግንባር እየፈጠሩ መምጣታቸዉ ወያኔን እንዳሳሰበዉና ከፉኛ እንዳስደነገጠዉም ታዉቋል። እንደብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ግምት ይህ ከሰሞኑ የታየዉ ከፍተኛ ወታደራዊ እንቅስቃሴም የዚሁ ድንጋጤ ዉጤት ነዉ የሚሉ ብዙዎች ናቸዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ አዲስ አበባን ጨምሮ በየክልሉ የነጻነት ኃይሎችን ለመቀላለቀል የሚደረገዉ እንቅስቃሴ እያደገ መምጣቱ ሌላዉ የወያኔ ስጋት ስለሆነ የሰሞኑ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የሚደረገዉ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ከመሀል የአገሪቱ ክፍሎች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የድንበር አካባቢዎች የሚወስዱ መንገዶችንና ኬላዎችን ለመዝጋት ነዉ የሚሉም አልታጡም። በዚህ ተኬደ በዚያ የሰሞኑ የወያኔ ወታደራዊ ሩጫ አላማዉ ባዕዳንን ለመከላከል ሳይሆን ለአገር አንድነትና ለህዝብ መብትና ነጻነት የሚታገሉ ኃይሎችን ለማፈን ነዉ።

## ወያኔ አዲስ አበባ ዉስጥ ቤት የማፍረስ ዘመቻ ዉን ተያይዞታል

መተካካት በሚለዉ ወያኔያዊ መመሪያ መሰረት በቅርቡ ኩማ ደመቅሳን በተካዉ በድሪባ ኩማ የሚመራው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት “የከተማዋን ነዋሪዎች ለመጥቅም’ በሚል ሰበብ መሃል አዲስ አበባ ዉስጥ በርካታ ቤቶችን ለማፍርስ በዝግጅት ላይ መሆኑ ተሰማ። በከንቲባ ድሪባ ኩማ የሚመራዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ሰሞኑን ባካሄደው ስብሰባ የከተማይቱን የአምስት ዓመት ዕቅድ ወደሁለት ዓመት ማጠፉ የተሰማ ሲሆን፤ እንዴት የሚለዉ ጥያቄ በፍጹም ባልተመለሰበት ሁኔታ ምክር ቤቱ በሚቀጥሉት ሁለት አመታት የነዋሪዎችን ተጠቃሚነት ያረጋግጣል ያለውንና በሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎችን ያለመጠግያ የሚያስቀረዉን “መልሶ ማልማት” የሚለዉን የወያኔ ዕቅድ በሰፊው እንደሚያከናውን አስታውቋል።በዚህ የመልሶ ማልማት ሥራ መሃል አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ በርካታ ቁልፍ ቦታዎች የሚፈርሱ ሲሆን ብዛት ያላቸዉ የከተማዉ ነዋሪዎችም የመፈናቀል አደጋ እንደተደቀነባቸዉ ተያይዞ የመጣልን ዜና ያስረዳል።

ምክር ቤቱ በ2006 እና በ2007 በጀት ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ዉስጥ በጥቅሉ ከ2 ሺህ ሄክታር በላይ ቦታ ለመልሶ ማልማትና ማስፋፊያ ስራዎች ለማዋል ያቀደ ሲሆን ቦታዎቹ ለጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ፣ ለንግድ ቦታዎች፣ ለኢንዱስትሪና ለመሳሰሉት በጨረታና በምደባ ስራ ላይ የሚውሉ ናቸው። ይሄዉ “መልሶ ማልማት” ከሚከናወንባቸው የአዲስ አበባ አካባቢዎች መካከል አራዳ ክፍለ ከተማ’ ደጃች ውቤ ሰፈር፤ አሜሪካን ጊቢ፤ አፍሪካ ህብረት ቁጥር 2 ፣ ቡልጋሪያ ኤምባሲ አካባቢና ለገሃር ዙሪያ ይገኙበታል። ከዚህ በተጨማሪ ልደታ ክፍለ ከተማና ከዚህ ቀደም በመልሶ ማልማት የኮንደሚኒየም ቤቶች ግንባታ ከተከናወነባቸዉ አካባበቢዎች አንዱ የሆነዉ ጌጃ ሰፈርም የዚሁ የወያኔ የማፍረስ ሴራ ሰለባዎች ሆነዋል።

ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት ፕራይቬታይዜሺን ፕሮክትን ጨምሮ ወያኔ የአገርና የህዝብ ልማት እያለ ተግባራዊ ባደረጋቸዉ ፕሮጀክቶች ሁሉ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቃሚ የሆኑት የህወሃት አባላት፤ ቤተሰቦቻቸዉና የወያኔ ታማኝ አሽከሮች እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ አይደለም። አሁንም ቢሆን በዚህ “መልሶ ማልማት” በሚባለዉ የወያኔ ዘመቻ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚተርፈዉ ነገር ቢኖር ከመሬቱና ከቤቱ መፈናቀል ነዉ እንጂ ተጠቃሚዎቹ ህወሃትና ግብረ አበሮቹ ብቻ ናቸዉ። ለምሳሌ በ1990ዎቹ በተካሄደዉ የፕራይቬታዜሺን ፕሮጀክት የህዝብና የአገር ንብረት የነበሩ ፋብሪካዎችንና የንግድና የማከፋፈያ ድርጅቶችን በርካሽ ዋጋ ገዝተዉ ዛሬ መጠን የለሽ ትርፍ የሚያጋብሱት “ኤፎርት” በሚል ምህጻረ ቃል በሚታወቀዉ የትግራይ ተራድኦ ድርጅት ስር የተሰባሰቡት የህወሃት ተቋሞች ናቸዉ። ጋምቤላ፤ ኦሮሚያና ኦሞ ሸለቆ ዉስጥ በተካሄደዉ የመሬት ቅርምት በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ የሆኑትም እነዚሁ በትግራይ ህዝብ ስም የተቋቋሙት የህወሃት ድርጅቶች ናቸዉ።

## ለሕዝባዊ ተቃውሞ የወያኔ ፈቃድ የማይጠየቅበት ቀን እንዲመጣ እንታገላለን!!!

መስከረም 19 ቀን 2006 ዓ.ም. አንድነት ለዲሞክራሲና ፍትህ ፓርቲ ከሌሎች በርካታ ፓርቲዎች ጋር በመተባበር የጠራው ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ተካሂዷል። ይህ ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ከዝግጅቱ እስከ ፍፃሚው ብቻ ሳይሆን ከፍፃሚው በኋላም በድርጊቶች የታጀበ ነበር።

ወያኔ ለሰልፉ እውቅና ሰጥቶ እያለ "መቀስቀስ አይቻልም፤ ፓስተር መለጠፍ አይቻልም፤ በዚህ ማለፍ፣ በዚያ መዞር አይቻልም" እያለ የፓርቲው መሪዎችን፣ አባላትንና ደጋፊዎችን ሲያስር፣ ሲፈታ፣ ሲያዋክብ ሰንብቷል። ይህም ሆኖ ግን የፓርቲ መሪዎች፣ አባላትና ደጋፊዎች ወከባውን ተቋቁመው ሰላማዊ ሰልፉን መጀመር ቻሉ።

ወያኔ ሰልፈኛው ወደ መስቀል አደባባይ እንዳይደርስ የለመደውን ጉልበት ተጠቀመ። ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይተሙ የነበሩ ሰላማዊ ሰልፈኞች እንዳይገናኙ በፓሊሶች ታገቱ። ኢትዮጵያ ውስጥ አፈና የደረሰበት ደረጃ ጎልቶ ታየ። ሰልፈኛው ሊደርስ ያሰበው ቦታ - መስቀል አደባባይ - መድረስ ሳይችል ቀረ። የሰልፉ አስተባባሪዎች የነበሩበት ብዛቱ በመቶ ሺህ የተገመተ ስብስብ ሊደርስ በቻለበት ቦታ የመዝጊያ ሥነሥርዓት ፈጽሞ ተበተነ።

የወያኔ ጆሮ ጠቢዎች ከሰልፉ በፊት፣ በሰልፉ ጊዜ እና ከሰልፉ በኋላ ግንባር ቀደም የሰልፉ ተዋንያንን የማደን፣ የማዋከብ፣ የማሠር፣ የመደብደብ "ሥራ" በዝቶባቸው ሰንብቷል። ባሠሩና ባዋከቡ መጠን ግን የሕዝብ ምሬት እየበረታ መጥቷል።

ወያኔ ሰልፉን ለመቆጣጠር እጅግ ብዙ የሆነ የፓሊስ፣ የጦርና የሰላይ ሠራዊት ለማሠማራት ተገዷል። ይህ ራሱ አንድ ድል ነው።

ከዚህ ሰልፍ የተገኘው ጥቅም ግን ይህ ብቻ አይለም። ወያኔ በሕዝብ ልብ ውስጥ ዘራሁት ያለው ፍርሀት በኖ የሚጠፋ መሆኑ፤ እድል በተፈጠረ ጊዜ ሁሉ ወጣቶች በፈጠራ ሥራዎቻቸው ተመልካችን ማስደመም የሚችሉ መሆኑን፤ የተለያዩ ሀይማኖቶች ተከታዮችን ለማጋጨት ወያኔ የሸረበው ድር የተበጣጠሰበት መሆኑ ሰልፉ አሳይቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ በወታደር እና በሰላዮች ብርታት ላይ የቆመ ሥርዓት መሆኑን አሳይቷል። ወያኔ በጠመንጃና በስለላ ላይ ያለው ሞኖፓሊ ካልተሰበረ ሕዝባዊ ተቃውሞዎችንም እሱ ከሚፈልጋቸው ክበብ እንዳይመጡ ማፈን የሚችል መሆኑ አሳይቷል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን የወያኔ ወታደራዊና የስለላ ሞኖፖሊ መስበር የሥራው አንድ አካል አድርጎ ይመለከታል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ አምባገነኑን ወያኔ በመገዳደር ላይ ያሉትን ወገኖች ትግል ያደንቃል። እንዳንዳንዳችን የየበኩላችን ጥረት ካደረግን የኢትዮጵያን የመከራ ጊዜ በእጅጉ እንደምናሳጥር ያምናል።

ግንቦት 7 ሕዝብ ተቃውሞ ለማቅረብ የወያኔን ባለሥልጣኖች ፈቃድ መጠየቅ የሚያበቃበት ጊዜ እንዲመጣ ተግቶ ይሠራል። ለዚህ ዓላማም ተባብረን እንድንቆምም ጥሪ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## አክሲስ ሪል ስቴት ኩባንያ የ72 ሚሊዮን ብር ክስ ተመሰረተበት

አዲስ አበባ ዉስጥ ከመገናኛ ወደ ቦሌ በሚወስደው ቀለበት መንገድ አካባቢ የአክሰስ ሪል ስቴት አክሲዮን ማኅበር አፓርትመንቶችን የገነባው ጋቢ ኢንቨስትመንት በመባል የሚታወቀዉ ኩባንያ የአፓርትመንቶቹ አሠሪ የሆነውን አክሰስ ሪል ስቴት ኩባንያን በ72.8 ሚሊዮን ብር ያልተከፈለ ዕዳ እንደከሰሰዉ ከአዲስ አበባ የደረስን ዜና አስረዳ::ጋቢ ኢንቨስትመንት አክሰስ ሪል ስቴት አክሲዮን ማኅበር ላይ የመሰረተዉን ክስ ያቀረበዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የፌዴራሉ ፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ክሱን ተቀብሎ ለስድስተኛ ፍትሐ ብሔር ምድብ ችሎት የመራዉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::

ጋቢ ኢንቨስትመንት ያቀረበው ክስ እንደሚያመለክተው፣ አክሰስ ሪል ስቴት የካቲት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. በቦሌ ክፍለ ከተማ ዉስጥ ለአፓርትመንት አገልግሎቶች የሚውሉ አምስት ብሎኮችን በ174.7 ሚሊዮን ብር ለመገንባት ሥራውን እንደተረከበ የሚታወቅ ሲሆን ይህ ዉል በተግባር ላይ እንዳለ በሚያዚያ ወር 2003 ዓ.ም የግንባታ ዋጋ ማሻሻያ ክለሳ ስምምነት በማድረጋቸው የግንባታ ዋጋው ወደ 224.13 ሚሊዮን ብር ከፍ ብሏል:: ከዚህ በተጨማሪ አክሰስ ሪል ስቴት ሌሎች ሦስት ብሎኮችን ገንብቶ እንዲያስረክበው ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም. የ108.3 ሚሊዮን ብር ውል ከጋቢ ኢንቨስትመንት ጋር ተፈራርሟል:: ጋቢ ኢንቨስትመንትና አክሰስ ሪል ስቴት ይህንንም ስምምነት በሚያዚያ 2003 ዓ.ም. በድጋሚ የማጠናቀቂያ ዋጋ ሳይጨምር የዋጋ ክለሳ ስምምነት አድርገው፣ የግንባታ ዋጋው ወደ 136.11 ሚሊዮን ብር ከፍ እንዲል ማድረጋቸው በክሱ ላይ ተገልጿል::

በጥቅሉ ጋቢ ኢንቨስትመንት ጠቅላላ ሥራውን ለማከናወን፣ አክሰስ ሪል ስቴት ደግሞ 360.24 ሚሊዮን ብር ለመክፈል መስማማቱንና አከፋፈሉም በየወሩ 20 ሚሊዮን ብር እንዲሆን ሁለቱ ኩባንያዎች ውል መግባታቸውን የቀረበው ክስ ያስረዳል:: የጋቢ ኢንቨስትመንት ክስ እንደሚያስረዳው፣ ግንባታውን ለማካሄድ የሚያስፈልጉትን የተለያዩ ዓይነት ግብዓቶች፣ ከባድና ቀላል ማሽነሪዎች፣ እንዲሁም አስፈላጊውን የሰው ኃይል አሰማርቶ ከተከፈለው በላይ ግንባታ ቢያከናውንም፣ አክሰስ ሪል ስቴት አልፎ አልፎ የተወሰነ ክፍያ ከመክፈል ውጭ በስምምነቱ መሠረትና በክፍያ ሠርተፊኬቱ ላይ በተገለጸው መጠን አለመክፈሉን ያስረዳል::

ጋቢ ኢንቨስትመንት በአምስት የመክፈያ ሠርተፊኬቶች ከተረጋገጠው 214.8 ሚሊዮን ብር ውስጥ አክሰስ ሪል ስቴት 25.8 ሚሊዮን ብር ካልከፈለ ውሉን እንደሚያቋርጥ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ክሱ ያስረዳል:: በማስጠንቀቂያው መሠረት አክሰስ ሪል ስቴት በአምስቱም የክፍያ ሠርተፊኬቶች የቀረበው የክፍያ ጥያቄ ሕጋዊና ትክክለኛ መሆኑን፣ ገንዘቡ በቀሪ ዕዳነት የሚፈለግበት መሆኑን በማመን፣ ገንዘቡን ከ10.5 በመቶ ወለድ ጋር በተቻለ ፍጥነት እንደሚከፍል ቃል በመግባት ግንባታው እንዲቀጥል በመማፀን እንደጠየቀ የጋቢ ክስ ያስረዳል:: ጋቢ ኢንቨስትመንት ይህን የአክሰስ ሪል ስቴት ቃል በማመን አምስት ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ሥራ በሁለት ተጨማሪ የክፍያ ሠርተፊኬቶች መሥራቱንና በአጠቃላይ የተሠራው የግንባታ ሥራ 220.02 ሚሊዮን ብር እንደደረሰ በክሉ ላይ አትቷል:: አክሰስ ሪል ስቴት ለጋቢ ኢንቨስትመንት በአጭር ጊዜ እከፍላለሁ ያለውን 25.8 ሚሊዮን ብር፣ እንዲሁም በሁለት የክፍያ ሠርተፊኬቶች የተጠየቀውን ገንዘብ እንዳልከፈለ የጋቢ ክስ ያስረዳል::

## ግንቦት7 የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አይነት የገቢ መሰባሰቢያ ዝግጅት እንደማይደርግ ገልጸዋል። በሌላ ዜና ደግሞ በርካታ ቁጥር ያላቸው ኖርዌ፤ ሲዉድንና በአካባቢዉ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ጋር እንደተወያዩ ለማወቅ ተችሏል። በዚህ ዉይይታቸዉ ወቅት አቶ አንዳርጋቸው የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ሃይልን ዓላማዎች፤ ተልዕኮዎችና ራዕይ በማስተዋወቅ ህዝባዊ ሃይሉ ከምስረታው ጀምሮ አሁን ድረስ ያለበትን ደረጃ በምስልና በጽሁፍ በተደገፈ ገለጻ ለተሰብሳቢው አቅርበዋል።

ከአቶ አንዳርጋቸው እስካሁን ድረስ የተካሄደዉ የህዝባዊ ኃይሉ ስልጠና የንቅናቄዉን የአመራር አካላት ያካተተ መሆኑን ጠቅሰዉ ወታደራዊ ስልጠናዉ የበታችና የበላይ የሚባል ልዩነት እንደሌለበት አስገንዝበዉ የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ሃይል የተመሰረተዉ ቤተሰባቸውን፤ ስራቸውን፤ገንዘባቸውንና የተደላደለ ኑሯቸውን ትተው ከኢትዮጵያና ከመላው ዓለም በተሰባሰቡ ኢትዮጵያውያን እንደሆነ እንደሆነ ገልጸዋል። የግንቦት ሰባት ዓላማ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ማስፈን ብቻ ሳይሆን ባለፉት 22 ዓመታት ኢትዮጵያውያን የተገፈፉትን ክብራቸውን ማስመለስ ጭምር መሆኑን አቶ አንዳርጋቸው አስምረውበታል።

## አገር ያለማል ተብሎ መሬት የተቸረዉ የህንዱ ካራቱሬ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የሰራተኞች ደመወዝ ክፍያ እስከ 45 ቀናት እንደሚዘገይ፣ ለጡረታና ለግብር ከሰራተኛው የሚሰበሰበው ክፍያ በአግባቡ ለሚመለከተው አካል እንደማይገባ አክለዋል። ከዚህ በተጨማሪ ግብርና ሚኒስቴር ባለፈዉ አመት ከራቱሬ ከወሰደዉ 800 ሺ ሄክታር መሬት ዉስጥ 200ሺ ሄክታር መሬት የነጠቀው መሆኑን አቶ አለምሰገድ አስታውሰው፣ ኩባኒያዉ ይህንንም ማልማት ባለመቻሉ በአሁኑ ወቅት በእጁ የሚገኘው መሬት 10ሺ ሄክታር ብቻ መሆኑን ተናግረዋል።የኩባንያው አመራር ኩባኒያዉ በውጪ ምንዛሪ የሚያስገባቸውን ዘርና ማዳበሪያ በአገር ውስጥ እንደሚሸጥና ከቀረጥ ነጻ ያስገባቸውን ማሽነሪዎች በማከራየትና ለሶስተኛ ወገን በመሸጥ ያልተገባ ጥቅም እንደሚያጋብስም አጋልጠዋል።

## ዘመነ ፍዳው እንዲያጥር ለምትፈልጉ ወገኖች ሁሉ! (ክፍል 1)

(ይነጋል በላቸው)

በየመን የኢትዮጵያ መንግሥት ተወካይ ስለኢትዮጵያውያን መሰቃየትና በ"ሀገራቸው ኤምባሲ" ሊረዱ እንደሚገባ ሲነገረው "እኛ እዚህ የመጣነው ለ‹ገረዶች› አይደለም" ማለቱን ከጋዜጠኛ ግሩም ተ/ሃይማኖት በኢሳት አማካይነት አሁን ሰማሁ - ጋዜጠኛ ግሩም እግዜር ይባርክህ - ዕንባህን ፈጣሪ ይመዝግብልንና ከሌሎች ዕንባዎች ጋር ተዳምሮ ጎርፍ በመሆን ወያኔን በቅርብ ይጠራርግልን:: በየመን የ‹ኢትዮጵያ› ኤምባሲ ተወካይ ሌላ ቃል ለጊዜው አጥቶ እንጂ ከዚያ በላይም ቢናገር ወያኔያዊ መብቱ ነው - ተፈጥሮው ስለሆነም ዛሬም ሆነ ነገ አይፀፅተውም፤ ካለተፈጥሮው እንዲሆን መጠበቅ ደግሞ ሞኝነት ነው:: ኢትዮጵያን ለማጥፋት ከተሾመ የወንበዴ መንግሥት ፍትህንና ወገንተኝነትን መጠበቅ ቂልነት መሆኑን በ22 ዓመታት ያልተረዳ ዜጋ፣ የማይሆን ጥያቄ ጠይቆ የማይሆን መልስ ቢሰጠው ሊገረም አይገባውም:: ከነተረቱ "ራሷ ሄዳ ጣፊያ የከለከሏት ‹ምላስ ሰምበር ላኩልኝ› አለች" ይባላል:: ወያኔ ከመነሻው ሀገርንና ዜጋን ድራሹን ለማጥፋት መነሳቱንና ይሄ ሁሉ ሕዝብ በዓለም ዙሪያ እንዲበተን ያስገደደው ራሱ ወያኔ መሆኑን እየተገነዘብን በራሱ አምሳል የተቀረጹ ድፍን ቅል ወያኔዎች የተሰገሰጉባቸው ነጋዴና የቢዝነስ ሥራ አቀላጣፊ ኤምባሲዎች መልካም ሥራ ይሠራሉ ብሎ መጠበቅ ከመነሻው ሞኝነት ነው - የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች የወያኔን እንጂ የኢትዮጵያን ጉዳይ አይፈጽሙም፤ አያስፈጽሙም:: የወያኔ ልጆችን የጦርና የቀለም ትምህርት ይከታተላሉ - መተካካቱ ችግር እንዳይገጥመው:: የወያኔ የሀብት ክምችት እምከን እንዳይገጥመው የዲፕሎማሲ ሥራ ይሠራሉ ... :: እርግጥ ነው ጋዜጠኛ ግሩም በመንታ በመንታ እያነባ የገለጠልን ሀገራዊ መራር እውነት በኢትዮጵያዊነታችን ፀንተን የቆየንና የሀገራችን ሰቆቃ የሌት እንቅልፍና የቀን የኅሊና ዕረፍት የሚያሳጣን ወገኖችን ማሳዘኑ፣ ማስለቀሱም አይቀርም:: ይህ ስቃያቸውና ስቃያችን እንደራሔል የራማ ጩኸት በፈጣሪ ዘንድ ተሰምቶልን የባርነታችንና የስደታችን የመከራ ዘመን እንዲያበቃ ሁላችንም ሁሉም ነገር ለማይሳነው አምላከ ኢትዮጵያ በርትተን መጸለይ ይገባናል:: ሙስሊሙም ለአላህ ይጸልይ - መንገዱ ቢለያይ መድረሻው አንድ ነውና ወይም ቢንስ አንድ እንደሚሆን በብዙዎች ይገመታልና ሁላችን ለየምናምንበት በመጸለይ ይህ የክፋት ዘመን ያለ ብዙ "ወጪ" ወደታሪክ መዝገብ እንዲካተት እንትጋ::

ኢትዮጵያውያን በስደት ያልገባንበት ሀገር እንደሌለ ይታወቃል:: ከሶሎሞን ደሴቶችና(Solomon Islands) ከሲሼልስ እስከ አላስካና ሳይቤሪያ በሁሉም የዓለም ግዛቶች እንደጨው ዘር ተበትነን አሣራችንን እየበላን እንገኛለን - የውርደት ውርደት ተዋርደን ከሰውነት በታች እስከመቆጠር በደረሰ አሰቃቂ ሁኔታ ላይም እንድንገኝ ታሪክ አስጠሊታ ብያኔውን አስተላልፎብን በሰውና በእንስሳነት ደረጃ መሀል እንገኛለን - ባገር ቤት ከምንገኘውም ብዙዎቻችን አንገታችንን ደፍተን በገዢው ጎጠኛ ቡድን እንደተዋረድን መኖራችን ግልጽ ነው - በነገራችን ላይ ዜጎች ለስደት የመከራ ሕይወት እየተጋለጡ የሚገኙት ‹ከሀገር ቤቱ የሚብስ የለም› ከሚል ተስፋ መቁረጥ እንጂ የግንዛቤ ችግር ኖሯቸው እንዳልሆነ ልጠቁም እፈልጋለሁ፤ ሁሉም ስደተኛ ባይባልም አብዛኛው በህገወጥ መንገድ በረሃዎችን አቋርጦ በደላላዎችና በድንበር አሻጋሪዎች በኩል ሲሰደድ ምን ሊደርስበት እንደሚችል ያውቃል - ሊገጥመው የሚችልን ጠባብ መልካም ዕድል ተጠቅሞ ሰው ለመሆን ሀገሩን ጥሎ እግሩ ባወጣው ይሰደዳል እንጂ ሌላው የሚዘገንን ነገር ሁሉ ይቅርና የሰው ልጅ ለመለዋወጫነት ሳይቀር እየዋለ እንደሆነ በስፋት በየሚዲያው ስለሚነገር ብዙው ሰው ይህን አያውቅም ማለት አንችልም:: ግን ምን ይደረግ? "ከወያኔ የሚብስ የለም!" በሚል ለዚህ ሁሉ ችግር መዳረጋችን ትልቅ የታሪክ ቅጣት ነው:: የምንከፍለው ዕዳ ስላለብን ሊሆን እንደሚችል በሚያመለክት መልኩ አበሳችን በዝቷል(ይህ ነገር አያልፍም ማለት አይደለም - በሚገባ ያልፋል - ልክ እንደዮዲት ጉዲትና እንደሌሎቹም የታሪክ ጉድፎቻችን ሁሉ):: ከሁሉም የሚገርመው ነገር አሰቃዮቻችንና አሳዳጆቻችን በመከራችን የሚደሰቱ መሆናቸው ነው:: እሱም ብቻ አይደለም:: አሳዳጆቻችን ከሀገራችን ሲያስወጡን የሚቀበሉን ሌሎች ‹የሰው ዘሮች› የበደልናቸው ሳይታወቅ በስቃያችን የሚደሰቱ መሆናቸው ነው:: ይህ ዓይነቱ በበርካታ የውስጥና የውጭ ኃይሎች የተቀነባበረ የሚመስል የስቃይ ዘመን ማብቃቱ ሳይታለም የተፈታ ቢሆንም ለአሁኑ ግን ልናምነው የማንችለው ትንግርት ሆኖብናል:: ከያቅጣጫው የምንሰማው ሀገራዊ ጉዳይ የሚያስደንቅና ከማስለቀስ አልፎ እንደማሽላዋ በእያረሩ መሳቅ በደረቁ እሚያስፈግግ እየሆነ ነው፤ አንገት ተቀልቶ ጭንቅላት ብቻውን እየተሽከረከረ ይስቃል እንደሚባለው መከራ በሚበዛ ጊዜ በትንሹም በትልቁም ሆድ ሲብሰን ክልብስ እያለ ጉንጮቻችንን የሚያርሰው ዕንባም ባቅሙ ይኮራብንና በምፀት እንስቃለን:: የኛም ነገር ሁሉም ነገራችን ዕንቆቅልሽ ሆኖብን እንደዚያው ሆነናል:: ... አሁን ላይ ሆነን ግን ወያኔን መውቀስና መሳደብ ኋላቀርነት ማለትም ጊዜ ያለፈበት ይመስለኛል:: የራስን ሥራ ሳይሠሩ ተፈጥሮው ወንጀልና ግፍንንና በደል መፈጸም ብቻ የሆነን አንድ አካል መልካም እንዲሆን ዘላለሙን መመኘት ከንቱነት ነው:: ወያኔ መልካም የመሆን ተፈጥሮ ቢኖረው ኖሮ ባሳለፉቸው 40 ዓመታት ገደማ ባሕርይውን በለወጠና ኢትዮጵያን ከተደጋጋሚ ውድመት ሊታደጋት በተቻለው ነበር:: አሁን አሁን ሳስበው ብዙዎቻችን እየጣርን ያለነው ድንጋይ ዳቦ እንዲሆን ወይም የእባብ ዕንቁላል እርግብ ሆኖ እንዲፈለፈል ነው:: የማይሳካ ነገር ስንመኝ ጥቂት የማይባሉ ወርቃማ ዐሥርት ዓመታት ላይመለሱ ነጎዱ፤ በዚህ ሂደት ግን መከራችንና ስቃያችን ጠርዝ እየለቀቀ በዓለም ፊት ውርደታችን እየከፋ መጣ:: እንደሰማሁት ሶማሊያውያን ሳይቀሩ በ‹መንግሥታቸው‹ና በራሳቸው መብትን የማስከበር ቆራጥነታቸው ሲከበሩ እኛ ብቻ በማንም እንደተዋረድን፣ እንደጠፍ አህያም ማንም የፈለገውን እንደጫነን አለን - ለዚህ ዘግናኝ ሀገራዊና ማኅበራዊ ሕይወት የዳረገንም በዋናነት ብዙዎቻችን በጥቅምና በዓላማ መለያየታችን እንዲሁም በሌሎች እየደረሰ የምናየው ችግር በእኛ ላይ ላለመምጣቱ እርግጠኞች የሆንን ያህል የወገኖቻችንን ችግር እንደራሳችን አድርጎ ያለማየት ወያኔያዊ ልክፍት ያሳደረብን አሉታዊ ተጽዕኖ ነው:: ከዚህ በላይ አሣፋሪና አስደንጋጭ ዘመን ከአሁን በፊት የደረሰብን ለወደፊቱም የሚደርስብን አይመስለኝም:: ገና ለገና በህጋዊ መንገድ አልወጣችሁም ተብሎ ይህን ያህል የወንጀለኞች አባሪና ተባባሪ የሆነ የኤምባሲ ሠራተኛ ሊኖረን የቻለው እቤት ያለው ‹መንግሥት› ፀረ-ኢትዮጵያ በመሆኑ እንጂ እነዚህ የኤምባሲ ሠራተኞች ቅንጣት ታህል የወገንተኝነት ስሜት ቢኖራቸው ኖሮ ችግራችን በአሣፋሪነቱ ያን ያህል ጎልቶ ሊወጣ የሚችል አልነበረም - በታሪክም በስመጥርነትም መቼም ከሱዳንና ከጅቡቲ አንሰን አይመስለኝም:: ድሃ መንግሥታት ዜጎቻቸው ይሰደዳሉ፤ ሠርተውም ለራሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለሀገራቸው ገቢን ያስገኛሉ - ህንድና ቻይና ሌሎችም የኤዥያ አህጉር ሀገሮች በዚህ ረገድ በጣም ይታወቃሉ:: የኛ ግን መንግሥት ተብዬውና ተሰዳጁ ወገን ዐይጥና ድመት ወይም በሬና አራጁ በመሆናቸው የመንግሥት ተጠሪዎች ለዜጎች ስቃይ መበርታት ደፋ ቀና ይላሉ እንጂ የዜግነት ይቅርና የሰብአዊነት ስሜት ፍጹሙን የላቸውም - ይህ ልዩነት የተፈጠረው የሌሎች ሀገሮች ባለሥልጣናት ዜጎቻቸውን - በህግም ሆነ አለህግ ቢሰደዱ - እንደዜጋ ሲቀበሉ ‹የኛዎቹ› ታሪካዊ ተልዕኳቸውን አይረሱምና ከሕዝቡ ጋርም ውኃና ዘይት መሆናቸውን ከጥንት ከጧቱ ይገነዘባሉና ማንም ተቀቀለ ወይ ተጠበሰ ምናልባት እንደባሕርይ አባታቸው እንደአቶ መለስ ዴቭላዊ ከመደሰት በስተቀር ደንታቸው አይደለም - መሬት የሚንከባለልን ኳስ ለማንሳት ያጎነበሰን የ12 ዓመት ሕጻን በተቃዋሚነት ፈርጆ ግንባሩን በጥይት ከሚበረቁስ አረመኔ ቅኚ ገዢ የወያኔ መንግሥት የተላኩና የጠባብ ብሔርተኝነት ደዌ የሚያሰቃያቸው ዕብድ ውሾች ለወገን ይቆረቆራሉ፣ ለሀገር ስምና ዝናም ያስባሉ ብሎ መጠበቅ፣ ምናልባትም በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቁሮች በጥቁሮች ላይ ያወጁትን ይህን በሀገራችን ግዘፍ ነስቶ የምናየውን ልዩ አፓርታይድ የሚያራምዱ ደናቁርት ወገኖችን የተለዩ ተፈጥሮ መዘንጋት ነው:: ‹ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ደግሞ ባለ ዕዳ አይቀበለውም›ና የነሱን ልበ-ደንዳናነት የተመለከተ የውጭው በተለይም በአጋንንታዊ መንፈስ የተነጠቀው ገንዘብ አምላኪ ዜጋ የነሱን መስመር ተከትሎ ያሰቃየናል፤ ያንገላታናል - እነዚህ ወገኖች ለተገፉና በበደል ጅራፍ ተገርፈው ከሀገራቸው ለሚሰደዱ ረዳት መሆን ሲገባቸው ከእንስሳነት ባሕርይም ወርደው የለዩላቸው አውሬዎች መሆናቸው ይበልጥ ያሳምማል - ቅጣት በየፈርጁ ሆነብን - "አንበሣን ፈርቼ ዛፍ ላይ ብወጣ ነብር ጠበቀኝ" እንዲሉ ነው - ግዴለም - ሊነጋጋ ሲል ይጨላልማልና ሁሉም ሽምቀቆዎች እንዲህ እንዳሁኑ መጠባበቃቸው ለበጎ ሳይሆን አይቀርም ብለን ተስፋችንን በፈጣሪ እናድርግ:: ግሩም ተ/ሃይማኖት እንዳለው በስስ የአካል ክፍሎቻችን የጋለ ብረት እየሰደደ በስቃያችን እስከመደሰት የደረሰ የሰው ዘር መኖሩን እየሰማን ነው:: በመንፈሳዊነት ዐይን ስናየው ይህ ሁሉ ከንቱነትና ጭካኔ የክፉ መንፈስ አምላኪነትንና ተከታይነትንም የማሳያ መንገድ ነው - በኛ መግነኑ ሆድ ያስብሳል እንጂ የዚህ ዓይነቱን ነገር መስፋፋት ከዱሮውም የምናውቀውና የምንጠብቀውም ነበር (ማቴ. ፳፬፣ የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ፩ - ከቁጥር ፲፰ ጀምሮ):: ክርስቶስ "የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ብሎ የጸለየላቸው ዓይነቶቹ እነዚህ የውጭና የሀገር ውስጥ አሳዳጆቻችንና አሰቃዮቻችን የመጨረሻውን ዋጋቸውን የሚያገኙበት ጊዜ በብርሃን ፍጥነት እየተወረወረ መምጣቱን ብንረዳም እስከዚያው ግን በተለይ በውጭ የሚገኙ የተቃዋሚ ኃይላትና ታዋቂ ግለሰቦች ሊያደርጉት የሚገባቸው ነገር መኖሩን መጠቆም እፈልጋለሁ:: ኅሊናየ ጠቁም ያለኝን ስጠቁም ጥቆማየን ለሚመከተው በማድረስ ረገድ ሚዲያዎች የተለመደ ትብብራቸውን እንደማይነፍጉኝ በማመን ምሥጋናየን ከወዲሁ አቀርባለሁ - ለነገሩ ማመስገን አለብኝ እንዴ? አዎ፣ ትግራይ አንላየን ይህችን ጦማር ካተመልኝ ማመስገን ሳይኖርብኝ አይቀርም - because it is a matter of being a reborn Ethiopian; nevertheless, um, one must be naive to expect such a U-turn, a radical move now; perhaps it is too early, or perhaps it will never happen due to ethnically oriented sociopathic infliction upon the structure of their seemingly dysfunctional brain. ... ይህ ድረገፅና አምሳያዎቹ ‹ዕድገታቸውን ጨርሰው› ከመክሰማቸው በፊት ነፍስ ማወቅ ከጀመሩ በርግጥም እሰዬው ነው ሊወደሱም ይገባቸዋል::... (አይ ይሄ ሆድ! ስንቱን አሳየን! የዋናዎቹስ ይሁን ግዴለም፤ እነገነት ዘውዴንና ክፍሌ ወዳጆን የመሰሉ አጋሰስ የተጋቦት ወያኔዎችን የጥፋት ተባባሪነት ታሪክ ስንታዘብ ስንትና ስንት ጉድ እኮ ነው እምናይ? ብርሃኑ ዘሪሁን በአንደኛው ገጹ ባሕርይው አማካይነት "ሆዳችን እንኳንስ ከኋላችን አልሆነ፤ ገፍቶ ገደል ይከተን ነበር!" ያለው እንዴቱን ያህል ትክክል ነው!? አሁን ሽመልስ ከማል አያሳዝናችሁም? - ለወያኔ ዕድሜ መርዘም ..... (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አንድነት ፓርቲ የእሁዱ የተቃዉሞ ሰልፍ አበራታችን ተስፋ ሰጪ ነዉ አለ

ባለፈዉ እሁድ መስከረም 19 ቀን አንድነት ፓርቲ ከ33ቱ ፓርቲዎች ጋር አዲስ አበባ ዉስጥ ያካሄደዉ ሰላማዊ ሰልፍ የኢትዮጵያ ህዝብ ምን ያህል ለዉጥ ለማየት እንደጓጓ ብቻ ሳይሆን ምን ያህል ወያኔንና ዘረኛ ስርዐቱን አንቅሮ እንደተፋ በግልጽ የሚያሳይ መሆኑን ሰልፉን የተመለከቱና በሰልፉ ላይ የተካፈሉ ሰዎች ተናገሩ። ወያኔና ቀጥረኞቹ ከእያንዳንዱ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማ ወደ መስቀል አደባባይ የሚወስደዉን መንገድ ሁሉ ዘግተዉ ወደ ሰልፉ የሚያመራዉን የአዲስ አበባ ነዋሪ ቢያስፈራሩም ህዝቡ ስድቡን፤ ዘቻዉንና ማስፈራሪያዉን ሁሉ ጥሶ ሰላማዊ ሰልፉን ተቀላልቅሎ የተቃዉሞ ድምጹን ሲያሰማ ዉሏል።

ከቅርብ ወራት ወዲህ ከህዝብ የሚቀርብበትን ከፍተኛ ተቃዉሞ ማስተናገድ ተስኖት ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር የአይጥና ድመት ጨዋታ የጀመረዉ የወያኔ አገዛዝ የዕርዳታ ገንዘብ የሚያስታቅፉትን ምዕራባዉያን አገሮች ለማስደሰት ብቻ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ትችላላችሁ ቢልም በተግባር ግን ሰልፉ እንዳይደረግ የደህንነትና የፖሊስ ኃይሉን በመጠቀም ይህ ነዉ ተብሎ የማይነገር ጫና በሰላማዊ ሰልፉ መሪዎችና በሰልፈኛዉ ላይ በማድረግ ላይ ነዉ። የወያኔ ደጋፊዎች መስቀል አደባባይን ጨምሮ ባሰኛቸዉ ግዜና ቦታ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ እየቻሉ ከእነሱ ጋር ሲተያዩ ቁጥራቸዉ በሚሊዮኖች የሚቆጠር የወያኔ ተቃዋሚዎች ግን መዉጪያና መግቢያዉ እየተዘጋባቸዉ "ጃን ሜዳ " ሂዱ መባላቸዉ ወያኔ ምን ያህል እመራዋለሁ ከሚለዉ ህዝብ ጋር መጣላቱንና ምን ያህል ህዝብን እንደሚፈራ የሚያሳይ ነዉ ሲሉ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ይተቻሉ።

መስቀል አደባባይ መሄድ ብንችል ኖሮ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ህዝብ ሰላማዊ ሰለፉ ላይ ሊገኝ ይችል እንደነበር ጥርጥር የለኝም ያሉት የአንድነት ፓርቲ ቃል አቀባይ አቶ ደንኤል ይህ በከፍተኛ አፈና ውስጥ የተካሄደው የተቃውሞ ሰልፍም ቢሆን ከ80 ሺ በላይ በሆነ ህዝብ መካሄዱ የተሳካና ለሚቀጥለው ሰልፍ ፍንጭ የሰጠ፣ ህዝቡ ለውጥ ፈላጊ መሆኑንና ከፓርቲያቸው ጎን የቆመ መሆኑን እንድናምን አድርጎናል ብለዋል።

የወያኔዉ ተላላኪ ሽመልስ ከማል በበኩሉ በሽብርተኝነት ወንጀል ተከሰው ፍርድ ያገኙና ፍርድ ለማግኘት የሚጠባበቁትን በአደባባይ መደገፍ የሚያስጠይቅ ወንጀል መሆኑን ጠቅሶ፣ የሚያመጣውን መዘዝ ለመቀበል ፓርቲዎቹ ዝግጁ መሆን አለባቸዉ **ቢልም ሽመልስ** የመናገር ነጻነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የማይገባዉ ወይም እሱ ብቻ እንደፈለገ መናገር የሚችል የሚመስለዉ የአስተሳሰብም የሂለናም ደሃ ሰዉ በመሆኑ እሱ በሚናገረዉ ተራ ንግግር መደናገጥና መዘናጋት ከኋላችን የተዉነዉ ታሪክ ነዉ ብለዋል።

## አርባ ምንጭ ዉስጥ ወያኔ አስሮ ከፈታቸዉ 39 ሰዎች 14ቱ ከስራቸዉ ተባረሩ

ደቡብ ክልል ቁጫ ወረዳ ዉስጥ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ በማንሳታቸዉና ጥያቄያቸዉን ይዘዉ ጠ/ሚኒስትሩ ቢሮ ድረስ በመሄዳቸዉ ብቻ አድማ መርታችኋዋል የሚል የፈጠራ ክስ ተመስርቶባቸዉ አርባ ምንጭ ዉስጥ እስር ቤት የተወረወሩ 40 ሰዎች ከሰሞኑ መፈታታቸዉን አርባ ምንጭ ሚገኙ የግንቦት ሰባት ምንጮች ዘገቡ። እነዚህ የክልሉ ፍርድ ቤት **ከእስር ከወራት በፊት ትዕዛዝ ያስተላላፈ ቢሆንም ለፍርድ ቤት ሳይሆን ለህግ አስፈጻማዉ ብቻ የሚታዘዘዉ ፖሊስ እስረኞቹን አልፈታም በማለቱ** ሰዎቹ ለተጨማሪ ወራት እስራትና እንግልት ተጋልጠዉ ቆይተዋል። ሰሞኑን ከተፈቱት ሰላሳ ዘጠኝ ሰዎች ዉስጥ አስራ አራቱ ወደ ስራ ገበታቸው ለመመለስ ወደ መስሪያ ቤታቸው ሲያቀኑ ስራ የለም የሚል የስንብት ደብዳቤ ተሰጥቷቸዋል።

ፍርድ ቤቱ እስረኞቹ እንዲፈቱ ያዘዘዉ ምንም አይነት ማስረጃ አልተገኘባቸወሁም በሚል ቢሆንም የሚሰሩበት መ/ቤት ግን በስራ ገበታችሁ ላይ አልተገኛችሁም ይህ ደግሞ እኛ መቀየር የማንችለዉ ከበላይ አካል የመጣ ትዕዛዝ ነዉ በሚል የራሱን ፍርድ ፈርዶባቸዉ ከስራ እንዳሰናበታቸዉ ከስራ የተባረሩት ሰዎች ለዘጋቢያችን ተናግረዋል።ከስራ ከተባረሩት መካከል አቶ ደፋሩ ዶሬ፣ አቶ ቲንኮ አሻንጎ፣ አቶ አማኑኤል ጎተሮ፣ አቶ ሳምበል ሸዋ፣ አቶ ባንቲርጉ ሄባና፣ መምህር መሸሻ ዜና፣ መ/ር ዶሌቦ ጎንጃ፣ ወ/ሮ ጊፍቲ ሰለማ፣ አተፐ እዮብ ጦና፣ አቶ አስፋው ይና፣ አቶ አሊሙሳ አርባ፣ አቶ አበራ ገ/መስቀል እና አቶ ዘውዴ ጎአ ይገኙበታል። የክልሉ አስተዳደር ከወራት በፊት ቁጫ ወረዳ ዉስጥ የተቀሰቀሰዉን ህዝባዊ ተቃዉሞ በማስተባበር የከሰሳቸዉን መቶ አለቃ ማሴቦ መዳልጮን አሁንም ከአስር እንዳልፈታ ዘጋቢዎቻችን አክለዉ የላኩልን ዜና ያስረዳል።

## የኢህአዴግ ባለስልጣናትን የሚያስተምረው ትምህርት ቤት ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ውዝግብ ውስጥ ገባ

ካለትምህርት ብቃታቸዉና ካለችሎታቸዉ ከወያኔ ጋር ባላቸዉ ንኪኪ ብቻ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን **የሆኑትን ሙሰኞች** የአመራር ሥልጠና በአገር ውስጥ የሚሰጠዉና ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ ኢንስቲትዩት በመባል የሚታወቀዉ ተቋም በትምህርት ሚኒስቴር ስር ካለውና የከፍተኛ ትምህርት ጥራትን ከሚከታተለዉ ኤጀንሲ ጋር ከፍተኛ ውዝግብ ውስጥ መግባቱ ተሰማ። ከአዲሰ አበባ የደረሰን ዜና እንደሚያስረዳዉ በኢንተርናሽናል **ሊደርሺፕ** ኢንስቲትዩትና በትምህርት ጥራት ኤጄንሲ መካከል ለተፈጠረዉ ዉጥረት መነሻዉ ተቋሙ ሳይፈቀድለት በዶክትሬት ዲግሪ **ከፍተኛ** ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር በመጀመሩ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ የሊደርሺፕ ተቋሙ ሳይፈቀድለት ተማሪዎችን በፒኤችዲ ዲግሪ መርሃግብር ተቀብሎ እያስተማረ መሆኑን በመጥቀስ ወቀሳ ያቀረበ ሲሆን የኢንስቲትዩቱ ፕሬዚደንት ፕሮፌሰር ባዕደግ በቀለ ግን ዕውቅና ያላገኙት በኤጀንሲው አቅም ማነስ መሆኑንና አቅም እስከንገነባ ድረስ ታገሱን መባላቸውን በመጥቀስ ወቀሳውን **ያስተባብላሉ**፡

ባለፈዉ ሳምንት ለህትመት በበቃዉ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ አስተያየታቸዉን የሰጡት ፕሮፌሰር ባዕደግ አንድ ተቆጣጣሪ አካል የሚቆጣጠራቸዉን ድርጅቶች በአግባቡ መቆጣጠር እንዲችል በአቅም **በለጦ** መገኘት ሲገባዉ እንዴት አቅም እስክገነባ ጠብቁኝ ይላል በማለት የኤጀንሲውን ትችት አጣጥለዋል። ኢንስቲትዩቱ ከ100 ኣመት በላይ ዕድሜ ካለውና በፊሊፒንስ አገር ከሚገኘው ቡልካን ስቴት ዩኒቨርሲቲ ጋር በመቀናጀት የሚሰጠው የፒኤችዲ ዲግሪ ዕውቅና እንዲሰጠው በ2004 ዓ.ም አመልክቶ ከአንድ ኣመት በኃላ አቅም አስከንገነባ ጠብቁ የሚል ምላሽ በማግኘቱ አዲስ ቅበላ ማቆሙን ማስተማር የጀመራቸውን ግን በውጪ አገርም ጭምር እያስተማረ መሆኑን በመጥቀስ የኤጀንሲውን ወቀሳ አጣጥለዋል።

## ዘመነ ፍዳው እንዲያጥር . . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ሲል ሆዱን ተመርኩዞ የሀሰት ምሥክርነቱንና ማስተባበያውን ለመስጠት እንዲህ ሲቅመደመድ ለታዘበው አንጀትን ይበላል - አይበላም? ቅን አሳቢ እንሁን - ይበላል። ከወያኔዎች በልጠው ወያኔን የሆኑ ሁሉ ስለሆዳቸውና ለሆዳቸው ሲሉ እንዲህ ሲሆኑ ስናይ ከምናዝንባቸው ይልቅ እናዝንላቸዋለን - ነገን የማየት ዕድላቸው በአንድ በኩልና በትንሹ በማፈርና ባለማፈር ተፈጥሯዊ ባሕርያቸው መካከል የተሸጎጠ በመሆኑ ምናልባት በጊዜ ሂደት አንጎላቸው በትክክል መሥራቱን የሚጀምር ከሆነ እንደግርማ አይገብሩ ወይም እንደ ንጉሤ አስገልጥ በዝጉብኞች ውስጥ በብርጭቆ ግርዶሽ ተደብቀው በሥነ ልቦናዊ ቀውስ እየተንገላቱ ቀባሪ እስከሚያጡ ድረስ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን አሰቃይተው በሞት እንዳይለዩን ከመጨነቅ ነው እንዲህ የምላችሁ - ቀዳሚውን አንድ ቢያውቅም። በሌላም ወገን አሁን በሚሠሩት ጠያፍ ነገር በህግም ሆነ በግንፍልተኝነት(ይህኛው ማንም ተበዳይ ነኝ የሚል ወገን ሊያስበው የማይገባ መጥፎ ነገር ነው!) ምን ሊደርስባቸው ከመገመት ውጪ ብዙዎቻችን የምናውቀው ነገር ባለመኖሩ ይህም ከአሁኑ እንድንንሰፈሰፍላቸው ያስገድደናል።)

በዐረብ ሀገራት የሚሰደዱ ወገኖቻችን የሚገኙበት አስቸጋሪ ሁኔታ ግልጽ ነው። ጊዜም የማይሰጠው ነው። ስለዚህ እንዲህ ብናደርግ ጥሩ ነው።

1. በውጪ የሚገኙ ተቃዋሚዎች ኅብረት ፈጥረው አንድ የዲፕሎማሲ ቡድን ይመሥርቱ። ይህ ቡድን በተለይ የዜጎቻችን ችግር አይሎ በሚታዩባቸው የዐረቡ ዓለም ጠንካራና ዓለም አቀፍ ተሰሚነት ያላቸውን ተወካዮችን ይላክ። የአሁኑ የኢትዮጵያ መንግሥት የሀገሪቱን ጥቅምና የዜጎችን መብት የማያስጠብቅ መሆኑን፣ ይልቁንም በተቃራኒው የሚሠራ ፀረ-ሰው መንግሥት መሆኑንና የሀገሪቱን ዘላቂና ቋሚ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅሞች ማስከበር የሚቻለው በሕዝብ የሚመረጥ መንግሥት ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑን በማስረዳት የእነዚህ ሀገራት መንግሥታትና ዜጎች በዚህ ክፉኛ እየተገፋ ባለ ሕዝብ ላይ ተጨማሪ ግፍና በደል እንዳይሠራ የተቻላቸውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ከሃይማኖትም ከሌሎች ማኅበራዊና ታሪካዊ ዳራዎችም በመነሳት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ይሠራ። የሀገሪቱ ሕዝብ እንደ አሁኑ ባለቤት እንደሌለው ሆኖ ለዘላለም እንደማይኖርና ባለቤት በሚኖረው ጊዜ መቀያየምን የሚፈጥር ጥቁር የታሪክ ጠባሳ እንዳያስቀምጡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች በጥንቃቄ እንዲያስቡበት በግልጽ ይነገራቸው። ሰዎች በፈጣሪ ፊት እኩል መሆናቸውንም እንዲያውቁት ጥረት ይደረግ። የሰው ግርድና ምርት እንደሌለው እንዲረዱ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ሥራ ይከናወን። በዚህ ረገድ ታዋቂ ኢትዮጵያውያንም የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ያድርጉ። ዝምታችን እያስጨረሰን ነውና በየፊናችን እየጮኸን ለወገኖቻችን ያለንን ፈጥኖ ደራሽነትና አለኝታነት እንግለጥ። ይህን ብናደርግ በታሪክም በፈጣሪም ዘንድ እንከበራለን። ባናደርግ እንወቀስበታለን። ( ክፍል 2 ሣምንት ይቀጥላል)

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org